የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በገዥው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# እስከመቼ

ጥር ፳፫ እስከ ጥር ፳፱ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
January 31 to February 6, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፫
Volume I Number 3

# የኢትዮጵያ ህዝብ የትግል አመራር

**በእስከመቼ ቁጥር ፩** አሁን ያለንበትን አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ተመልክተን፤ እኛ በውጭ ሀገር የምንኖር ኢትዮጵያዊያን፤ በንቁ ለመሣተፍ መነሣታችንን አበሰርን።

**በእስመቼ ቁጥር ፪** ደግሞ፤ ተባብረን በአንድ ግንባር መታገል ማስፈለጉን በህዝቡና በድርጅቶች ደረጃ ዕመነቱ ኖሮ፤ ለመተባበር በመታገል ጊዜ ማጥፋታችንን አስመልክተን፤ እኛ በዚሁ የህዝባችን ትግል ድርሻችንን ለማበርከት አመቺና ውጤት ሊያስገኝ ይችላል የምንለውን መንገድ ለመምረጥና ምርጫችንን በዚች በእስከመቼ ቁጥር ሶስት ልናሳውቃችሁ ቃል ገባን።

በዛሬዋ **የእስመቼ ቁጥር ፫**፤ በመጀመሪያ ትግሉ ያለበትን የአሁን ደረጃና ለደረስንበት ምርጫ የመራንን መንገድ እናብራራለን። ቀጥሎም ምርጫችንን እናሳውቅና በመጨረሻ ይኼንኑ ምርጫችንን አስመልክቶ፤ መደረግ ያለበትን ጥንቃቄ እናሰምርበታለን። ግሩም።

## የትግሉ ደረጃ

የገዢው ክፍል ዕድሜውን ለማራዘም፤ የፖለቲካ ፍልስፍናው መሠረትና የአሥተዳደር ልጓሙ መመሪያ የሆነውን የከፋፍለህ ግዛ ማደናበሪያ በሠፊው ተያይዞበታል። በአሁኑ ወቅት፤ የተቃዋሚዎቹን ወገን ለማበጣበጥም ይኼንኑ ዘዴ ተጠቅሞበታል። ይህ ማናችንንም አያስደንቀንም። ይኼን ለመገንዘብ ከአዋቂ ሠፈር መሄድ አይጠይቅም። ጥያቄው በታጋዩ ወገን ያለው ግንዛቤና መልስ ነው። መልካም። ወደዚያ እንሂድ።

ያለምንም ማንቋለጳጰስ፤ **ትግሉ መሪ አጥቷል።** እንደሰመመን ብልጭ ድርግም ባይ ዕይታዎችን አንፀባርቆ እንደሆን እንጅ፤ **ከመጀመሪያው ጀምሮ፤ ይህ ትግል፤ መሪ አልነበረውም።** ትግሉ የተወለጋገደ ጉዞውን እስካሁን ያደረገው የገዥው ቡድን በሚወረውርለት አጀንዳ እንጅ፤ የህዝብ ክፍል የሆነው ወገን፤ አንድ ዕርምጃ ከህዝቡ ፊት ቀድሞ፤ አመራር ሠጥቶት አይደለም። እናም ማዕከልና መሪ የሌለውን ትግል፤ ጥሩ ውጤት እንዲያስገኝ መጠበቅ፤ ***ላም አለኝ በሰማይ*** ነው።

ቀጥሎም የተገነዘብነው፤ መበታተንንና እርስ በርስ መጎነታተልን ነው። እርስ በርስ የሚዋጋ ሠራዊት ጠላቱን አቸንፎ፤ በድል አድራጊነት የወጣበት ሂደት በታሪክ አልተመዘገበም። የተቃዋሚ ድርጅቶችን ***"እኔ አምር እኔ አምር"*** መሙሸርሸር አንድ ወዳጃችን፤ ***"የሌሎችን ኃጢያት ሁሌ ሲዘረዝር የሚኖር እርሱ ሊፀድቅ አይችልም።"*** በማለት፤ አሳምሮ አስቀምጦታል።

ትግሉ ያለበትን ደረጃ እንዲህ ካስቀመጥን በኋላ፤ የያንዳንዱን ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም አጥንተናል። የእስካሁን ታሪካቸውን ተመልክተናል። በአሁኑ ሰዓት ያላቸውን የሀገሪቱ የአሁን የፖለቲካ አቋማቸውና መፍትሄ ብለው ያመኑበትንና ያቀረቡትን ተከታትለናል።

## ምርጫችን

ብዙ ጉድለቶች አሉት። ብዙ መስተካከሎችን ይጠይቃል። ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ሀገር ውስጥ የተፈጠረው መድረክ ጥሩ ጅምር ነው። ብዙ ጠንካራ ጎኖች አሉት። መሠረታዊ የሆኑትን፤ ማለትም፤ የህዝቡን የመብቱ ባለቤትነት፤ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና አንድነት፤ እና የሕግን የበላይነት የተቀበለ ነው። እናም ደጋፊዎች ሆነን፤ መስተካከል ያለበትን እየጠቆምንና እንዲስተካከሉ ለሚመለከታቸው እያቀረብን፤ ስብስቡን ለማጠንከር ወስነናል። ለምን እስከአሁን ደጋፊዎችን የሚያሰባስብ በውጭ እንዳላቋቋሙ ግልፅ ባይሆንልንም፤ እኛ ከዚህ ኃላፊነቱን በመውሰድ፤ ጠንካራ የመድረኩ ደጋፊ ድርጅት ለመመሥረት ቆርጠን ተነስተናል።

## መደረግ ያለበት ጥንቃቄ

ዋናው የመድረኩ ዓላማ፤ ሀገራችን ከተጠመደችበት ማነቆ እንድትላቀቅ፤ የህዝቡን የመብቱ ባለቤት መሆን በራሱ ድምፅ ለማረጋገጥ እንጅ የግል ተመራጮችን ቁጥር በፓርላማ ለማብዛት መሯሯጫ መሆን የለበትም።

ድርጅታዊ ብቃትና ጥንካሬ የሚኖረው በዕኩልነት ሁሉን ባሳተፈና ባስተባበረ መልክ ሲሠራ ነው። አንዱ ድርጅት፤ ጀማሪ ነኝ፣ ጠሪ ነኝ፣ ትልቅ ነኝ፣ ነባር ነኝ በማለት በብልጣ ብልጥነት ራስን በግል ለመጥቀምና ሌሎችን ለመጨፍለቅ መሞከር አፍራሽ ነው። ይህ አብዛኞቹን አባል ድርጅቶች መረማመጃ ሆነው ለአንዱ ድርጅት ድርጅታዊ መስዋዕትነት እንዲከፍሉ መጠየቅ ነው። በሌላው በኩል ማንም ድርጅት ለአፍራሽ ሠርጎ ገቦች ቀዳዳ ከፍቶ ስብስቡ እንዲፈርስ ማድረግ የለበትም። በተጨማሪም፤ ***"የዚህ ክልል ተወካይ እኔ ብቻ ስለሆንኩ እዚህ አትድረሱ ብሎ ማካለል አፍራሽ ነው።"*** ይልቁንስ ተቀራራቢ ድርጅቶች እንዲዋሃዱ ማበረታታት ነው።

**የእስከመቼ ዕትም**
**የዝግጅት ቦርድ፤**
ድረስ ነጋ
ሕሊና ነጋሣ
እና ሀገሬ ተመቼ
eske.meche@yahoo.com